በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

አሐዱ አምላክ

- ነገረ ሃይማኖት መግቢያ

- “ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፊጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።” ይሁዳ ቁ. 3

ሃይማኖት

- አሚን (አምነ)፡- ማመን ፣መቀበል ፣ተስፋ ማድረግ፣አለመጠራጠር፣መናዘዝ እውነት መናገር፣ መመስከር ብለው ይፈቱታል። ኪዳነ ወልድ ገጽ226
- ሀይመነ ፤ አመነ ፣ታመነ ፣
- ሃይይኖት በቁሙ፡- ማመን መታመን፣ እምነት፣ጽኑእ ተስፋ፣የአምልኮ ባህል፣ በልብ፣ በረቂቅ ሐሳብ የሚሳል ማለት ነው።
- ሃይየኖት ቅስድት፡- ምሥጢረ ሥላሴ፣ምሥጢረ ሥጋዌ...
- ሃይማኖት ርትዕት፡- ኦርቶዶክሳዊት ፣የኦርቶዶክስ ባሕል
- ኪዳነ ወልድ ገጽ 369

ሃይማኖት

- እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጅ የገለጠው መግለጥ ነው።
- የሰው ልጅ ሊቀበለው በሚችለው መጠን እግዚአብሔር ስለ ራሱ ማንነት ለእኛ የገለጠው እውነታ ነው።
- “የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤” ዮሐ. 16፡12-13

- ሃይማኖት መንገድ ነው።
- “ነገር ግን፦ ቃሌን ስሙ፥ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ፤ መልካምም ይሆንላችሁ ዘንድ ባዘዝኋችሁ መንገድ ሁሉ ሂዱ ብዬ በዚህ ነገር አዘዝኋቸው።” ኤር. 7፡23
- “የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ” መዝ. 15፡11
- “እነዚህን አሥራ ሁለቱን ኢየሱስ ላካቸው፥ አዘዛቸውም፥ እንዲህም አለ፦ በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ” ማቴ. 10፡5

- “ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።” ዮሐ. 14:6
- “በዚህ መንገድ ያሉትንም ሰዎች ወንዶችንም ሴቶችንም ቢያገኝ፥ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው ዘንድ በደማስቆ ላሉት ምኩራቦች ደብዳቤ ከእርሱ ለመነ።” የሐዋ. 9፡2
- “ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን፥ የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ።” ያዕ. 5፡20

ለሃይማኖት መታዘዝና መጠበቅ ይገባል

- “የሰይጣን ዙፋን ባለበት የምትኖርበትን አውቃለሁ፤ ስሜንም ትጠብቃለህ፥ ሰይጣንም በሚኖርበት፥ በእናንተ ዘንድ የተገደለው የታመነው ምስክሬ አንቲጳስ በነበረበት ዘመን እንኳ ሃይማኖቴን አልካድህም።” ራእ. 2፡13
- “እንግዲህ በሰማያት ያለፉ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።” ዕብ. 4፡14
- “መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ” 2 ጢሞ. 4፡7

ሃይማኖት ስንት ነው

- “አንድ ጌታ፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት” ኤፌ. 4፡5-6
- “ወዳጆች ሆይ፥ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን ልጽፍላችሁ እጅግ በተጋሁ ጊዜ ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ ።” ይሁዳ 3
- እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ፣ ባሕርዩም የማይለወጥ ስለ ሆነ ሃይማኖት አንድና የማይለዋወጥ ነው።

ሃይማኖት ለምን አንድ ብቻ ሆነ

- 1. ስለ አንድ ነገር ሊኖር የሚችለው እውነት አንድ ብቻ ስለሆነ፤
- 2. እግዚአብሔር ባሕርዩ አንድና የማይለወጥ ስለሆነ፤
- 3. እግዚአብሔር የተናገረው ቃሉ እውነት ስለሆነ

የሃይማኖቶች ልዩነት

	ክርስትና	አይሁድ	እስልምና	ሂንዱይዝም	ቡድሂዝም
እግዚአብሔር	አንድነት በልዩ ፫ነት	፮ ገጽ	፮ ገጽ	ብዙ ናቸው(ብራህማ፣ ቪሽኑ፣ ሺቫ)	ምንም የለም
ኢየሱስ ክርስቶስ	የእግዚአብሔር ልጅ ነው።	አይደለም	አይደለም	--- ---	--- ---
የዚህ ዓለም ሕይወት ዓላማ	የአሁኑና የሚመጣው	የሚመጣው	የሚመጣው	ከብዙዎቹ አንዱ ነው	ይህ ብቻ ነው
ከሞት በኋላ	ከሞት በኋላ ገነት/ሲኦል	መ/ሰማያት/ ገሃነም	መ/ሰማያት/ ገሃነም	ደግሞ ሰው መሆን (Reincarnati on)	ኒርቫና

የቀጠለ

	ኦርቶዶክስ	ፕሮቴስታንት	ጀሆቫ ምስክር	አድቬንቲስት
ኢየሱስ ክርስቶስ	አምላክ ነው።	አምላክ ነው፣ አማላጅም ነው።	አምላክ አይደለም	
መዳን	የሚያድግና ሂደታዊ	ቅጽበታዊ	በዚህ ዓለም	
ም.ጥምቀት	ለመዳን ያስፈልጋል	አያስፈልግም	አያስፈልግም	አያስፈልግም
ም. ቁርባን	አማናዊ ነው	አማናዊ አይደለም	አማናዊ አይደለም	አማናዊ አይደለም

- “እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል።” ማቴ. 5፡19

ብዙ ሃይማኖቶች ከየት መጡ

- “ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ፦ መንግሥተ ሰማያት በእርሻው መልካም ዘርን የዘራን ሰው ትመስላለች። ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ።
- “ስንዴውም በበቀለና በአፈራ ጊዜ እንክርዳዱ ደግሞ ያን ጊዜ ታየ። የባለቤቱም ባሮች ቀርበው። ጌታ ሆይ፥ መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ አልነበርህምን? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ? አሉት።
- “እርሱም፦ ጠላት ይህን አደረገ አላቸው። ባሮቹም። እንግዲህ ሄደን ብንለቅመው ትወዳለህን? አሉት።

- ፡፡ “እርሱ ግን፦ እንክርዳዱን ስትለቅሙ ስንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትነቅሉት አይሆንም፤ ተዉአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ፤ በመከር ጊዜም አጫጆችን። እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ÷ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ አለ።” ማቴ. 13፡24-30
- “በዚያን ጊዜ ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ። ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው የእርሻውን እንክርዳድ ምሳሌ ተርጕምልን አሉት።
- “እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤ እርሻውም ዓለም ነው፤ መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤ እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው÷ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፤ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው÷ አጫጆችም መላእክት ናቸው።

- “እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል÷ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል። የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል÷ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፣ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።” ማቴ. 13፡36-43
- “በእናንተ ዘንድ የተፈተኑት እንዲገለጡ በመካከላችሁ ደግሞ ኑፋቄ ሊነሣ ግድ ነውና።” 1 ቆሮ. 11፡19
- “መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ÷ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል” 1 ጢሞ. 4፡1-2

- “ . . . እንዲህም የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ ደግሞ እንደ ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ÷ በመልእክቱም ሁሉ ደግሞ እንደ ነገረ ስለዚህ ነገር ተናገረ።
- በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ÷ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣመሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ። እንግዲህ እናንተ÷ ወዳጆች ሆይ÷ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ÷ በዓመፀኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ” 2 ጴጥ. 3፡15-17
- “ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና÷ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስቱ ዘንድ ምልክትና ድንቅ ያደርጋሉ።” ማር. 13፡22
- “ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ” 2 ጴጥ. 2፡1

- “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ÷ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ።” የሐዋ. 20፡28-30
- “በእውነቱ የስህተት ትምህርት ወዲያውኑ ታይቶና ታውቆ እንዳይገለጥ ርቃኑን ከቶ አይቆምም። ነገር ግን መስህብነት ያለውን ልብስ በብልሃት ለብሶ በውጭ አምሮ ይገኛል። የሚሞኝ ሰው ካገኘ ለማታለል ከእውነትም የበለጠ እውነት መስሎ ይታያል።” ቅዱስ ሄሬኔዎስ

ሃይማኖት እንዴት ተገኘ

- “ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።” ይሁዳ 3
- በአምላካዊ መገለጥ (Divine Revelation) ብቻ ነው።
- “ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።” ማቴ. 16፡17 - አብ ሲገልጥ “ስለዚህ፥ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፥ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ” ዕብ. 3፡1

- ፡፡ “መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።” - መንፈስ ቅዱስ ሲገልጥ 1 ቆሮ. 2፡10
- ስለዚህ ሃይማኖት የተገለጠው በቅድስት ሥላሴ ነው ማለት ነው።
- “የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት” ዮሐ. 17፡8
- “እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ” 1 ቆሮ. 15፡3

ስለዚህ ሃይማኖት

- ተሐድሶ ወይም ለውጥ አያስፈልገውም ።
- ሃይማኖትን ይቀበሉታል፣ ይጠብቁታል፣ ያወርሱታል እንጂ ላድሰው፣ ላሻሽለው አይባልም፤
- እንዲያ ከሆነ መጀመሪያ የተሰጠው ሃይማኖት ሕፀፅ ነበረበት፣ ወይም ምሉዕ አልነበረም ያሰኛል።
- እግዚአብሔር የሰጣት፣ አባቶቻችን ከእርሱ ተቀብለው ለእኛ ያወረሱን ሃይማኖት ግን ፍጽምትና አንድ ጊዜ የተሰጠች ናት።
- ብልየት እርጅና የለባትም፣ እድሳት የሚለው ቃሉ ራሱ ብላሽና ለሃይማኖት ሊነገር የማይችል ጸያፍ ነው።

የክርስትና ሃይማኖት

- የክርስትና ሃይማኖት በሰዎች የተመሠረተ ሃይማኖት አይደለም።
- እንደዚሁም ክርስትና ድሮ ሳይኖር ቀርቶ በኋላ በሆነ ዘመን ላይ የመጣ ሃይማኖትም አይደለም።
- የክርስትና ሃይማኖት እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ ከሰው ልጆች ጋር የነበረው ግንኙነት ነው። ከያም ባሻገር ከሰው መፈጠር በፊት ከነበሩት ከመላእክት ጋር የነበረው ግንኙነትም ነው።
- “በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።” ዘፍ. 3፡15

- “እንግዲህ እንደ ወንጌሌ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም እንደ ተሰበከ÷ ከዘላለም ዘመንም የተሰወረው፤ አሁን ግን የታየው፤ በነቢያትም መጻሕፍት የዘላለም እግዚአብሔር እንደ አዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ የታወቀው ምሥጢር እንደ ተገለጠ መጠን . . .” ሮሜ 16፡25-26
- “ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለ ጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ÷ ሁሉንም በፊጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለኔ ተሰጠ።” ኤፌ. 3፡8-9

- “በበሰሉት መካከል ግን ጥበብን እንናገራለን÷ . . . ተሰውሮም የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን።” 1 ቆሮ. 2፡6-8
- “ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው÷ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጧል። ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፤ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው” ይላል። ቆላ. 1፡26-27
- ለምሳሌም ቅዱስ ወንጌል የመዘገባቸውን ሁለት ሰዎች መመልከት ይቻላል፡- አረጋዊው ስምዖን እና ነቢዪቱ ሐና።

- የጌታን መወለድ ስላየችውና እግዚአብሔርን ስላመሰገነችው ስለ ነቢዪቱ ሐና ደግሞ እንዲህ ይላል።
- “ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢዪት ነበረች፤ . . . በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር። በዚያችም ሰዓት ቀርባ እግዚአብሔርን አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ እርሱ ትናገር ነበር።” ሉቃ 2፡36-38

ትንቢት (በብሉይ	ፍጻሜ (በሐዲስ ኪዳን)
1 “በአንተና በሴቲቱ መካከል÷ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፣ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል÷ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።” ዘፍ. 3፡15 2 “አምላክህ እግዚአብሔር በዚያ ስሙ ይጠራበት ዘንድ በመረጠው ስፍራ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ከበግና ከላም መንጋ ፋሲካ ሠዋ።” ዘዳ. 6:2	“ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ” ገላ. 4፡4 “ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና” 1 ቆሮ. 5፡7 “ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ÷ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።” ዮሐ. 1፡29
3.“ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።” ኢሳ. 7፡14	“ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ÷ ድንግል ትፀንሳለች÷ ወንድ ስለዚህ ልጅም ትወልዳለች÷ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።” ማቴ. 1፡ 21-23
4. “የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ለሕዝብ ሁሉ በዚህ ተራራ ላይ ታላቅ የሰባ ግብዣ÷ ያረጀ የወይን ጠጅ÷ ቅልጥም የሞላባቸው የሰቡ ነገሮች÷ የጥሩና ያረጀ የወይን ጠጅ ግብዣ ያደርጋል።” ኢሳ. 25፡6	“መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች። የታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ ባሮቹን ላከ፣ ሊመጡም አልወደዱም። ደግሞ ሌሎችን ባሮች ልኮ የታደሙትን፡- እነሆ ድግሴን አዘጋጀሁ፣ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፣ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ።” ማቴ. 22:2-4
5.“እግዚአብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፣ የወይን ስካር እንደ ተወው እንደ ኃያልም ሰው” መዝ. 5፡2	“እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ።” ማቴ. 2፡3-6

6.	“አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ÷ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ÷ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።” ሚክ. 5፡2	እርሱም÷ አንቺ ቤተ ልሔም÷ የይሁዳ ምድር÷ ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሽም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተ ልሔም ነው አሉት።” ማቴ. 2፡36 41
7.	“የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ለሕዝብ ሁሉ በዚህ ተራራ ላይ ታላቅ የሰባ ግብዣ÷ ያረጀ የወይን ጠጅ÷ ቅልጥም የሞላባቸው የሰቡ ነገሮች÷ የጥሩና ያረጀ የወይን ጠጅ ግብዣ ያደርጋል።” ኢሳ. 25፡6	“መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች። የታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ ባሮቹን ላከ፤ ሊመጡም አልወደዱም። ደግሞ ሌሎችን ባሮች ልኮ የታደሙትን፦ እነሆ ድግሴን አዘጋጀሁ፤ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፤ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ።” ማቴ. 22:2-4
8.	“እግዚአብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፤ የወይን ስካር እንደ ተወው እንደ ኃያልም ሰው” መዝ. 5፡2	“እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ።” ማቴ. 2፡3-6
9.	“አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ÷ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ÷ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።” ሚክ. 5፡2	እርሱም÷ አንቺ ቤተ ልሔም÷ የይሁዳ ምድር÷ ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሽም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተ ልሔም ነው አሉት።” ማቴ. 2፡36 41

- “እርሱም፦ እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው። ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።” ሉቃ. 24፡25-27
- “እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ፤ የሚከሳችሁ አለ፤ እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው። ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?” ዮሐ 5፡4547

- ስለ አረጋዊው ስምዖን እንዲህ ይላል፡-
- “በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር። በመንፈስም ወደ መቅደስ ወጣ፤ ወላጆቹም እንደ ሕጉ ልማድ ያደርጉለት ዘንድ ሕፃኑን ኢየሱስን ባስገቡት ጊዜ፥ እርሱ ደግሞ ተቀብሎ አቀፈው። እግዚአብሔርንም እየባረከ እንዲህ አለ፦
- “ጌታ ሆይ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፤ ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን፣ ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው። . . .።” ሉቃ. 2፡26-35

- “ወንድሞች ሆይ፥ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፤ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፥ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ።” 1 ቆሮ. 10፡1-4
- ጌታችን “ውስተ ርእሰ መጽሐፍ ተጽሕፈ በእንቲአየ - በመጽሐፍ ራስ (በመጀመሪያው መጽሐፍ) ስለ እኔ ተጽፏል” ያለው ለዚህ ነበር።

“የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ፥ ጐብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጓልና፤ ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደ ተናገረ፥ በብላቴናው በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነስቶልናል፤ ማዳኑም ከወደረኞቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው፤ እንደዚህ ለአባቶቻችን ምሕረት አደረገ፤ ለአባታችን ለአብርሃምም የማለውን መሐላውን ቅዱሱን ኪዳን አሰበ።” ሉቃ. 1፡68-73

- “እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም” ያለው ለዚህ ነው። ማቴ. 5፡17

- “ለእናንተም ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፤ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ፥ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ፥ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር።” 1 ጴጥ. 1፡10-11
- “ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና።” ሮሜ

- “አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና። እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ።” ዮሐ. 4፡37-38
- ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እንደ ኦሪቱ ሕግ መሠረት የሃይማኖት በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሲመለስ ከነቢያት መጻሕፍት አንዱ የሆነውንና ይጠበቅ የነበረውን ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ የተነገረውን ክፍለ ምንባብ እያነበበ ነበር።
- ያነበው የነበረው የመጽሐፉ ክፍልም ይህ ነበረ:-
- “እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፥ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፤ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና፣ ትውልዱንስ ማን ይናገራል?”

- ያን ጊዜ ጃንደረባውም ለፊልጶስ መልሶ፦ “እባክህ፥ ነቢዩ ይህን ስለ ማን ይናገራል? ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለ ሌላ?” ብሎ ጠየቀው።
- “ፊልጶስም አፉን ከፈተ፥ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት። በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውኃ ደረሱ፤ ጃንደረባውም። እነሆ ውኃ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው?” አለው።
- ፊልጶስም “በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዷል” አለው። መልሶም፦ “ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ” አለ።
- ከዚያም “ጃንደረባውም ሰረገላው ይቆም ዘንድ አዘዘ፥ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ፥ አጠመቀውም። ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው፤ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፥ ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና።” የሐዋ. 8፡26-39

- ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በሐዋርያው በቅዱስ ፊልጶስ የተሰበከለትና ያመነው ነገር አዲስ ነገርን (በፊት ይጠበቅ ያልነበረ አንግዳ ነገርን) አልነበረም።
- እርሱም በናፍቆት ይጠብቀው የነበረ ነገር ስለ ነበር ወዲያውኑ አምኖ ተጠምቆ የተስፋው ፍጻሜ እንጂ አዲስ ነገር ያልሆነውን የምሥራች (ክርስትናን) ይዞ ወደ አገሩ መጥቷል። 50
- ክርስቲያን ማለት የክርስቶስ ወገን የሆነ፣ በክርስቶስ የሚያምን፣ የክርስቶስ ተከታይ ማለት ነው።
- “ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።” የሐዋ. 11፡26 “ባሪያዎቹንም በሌላ ስም ይጠራቸዋል።” ኢሳ. 65፡15 እስራኤል = የእግዚአብሔር ሕዝብ

ኦርቶ ዶክስ

- Orthos right) (ቀጥተኛ) and
- doxa (teaching or worship) አስተምህሮ ወይም እልኮት ሃይማኖት
- እውነተኛ አስተምህሮ (right teaching)፣
- እውነተኛ አምልኮ (right worship) ማለት ነው።
- በጥንቱ የክርስትና ዘመን ክርስቲያን ነን የሚሉ የስህተትና የኑፋቄ ትምህርቶች እየበዙና የቤ/ክንን አንድነትና ንጽሕና ሊሸፍኑ ስለ ደረሱ ሐዋርያዊት የሆነችውን እምነትና አስተምህሮ ከሌሎቹ ለመለየት “ኦርቶ ዶክስ” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ዋለ።

- ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ከጌታና ከሐዋርያት የተቀበለችውን እውነት በፍጹም ጥንቃቄ ትጠብቃለች፣ ይህም መንጋዋን ለመጠበቅ እና እርሷ አካሉ የሆነችለትን ራሷን ክርስቶስን ለማክበር ነው።
- ለቀደምት አበው ኦርቶዶክሳዊነት “ርትዕት እምነት” በሚለው ትርጉም ብቻ የተወሰነ አልነበረም፤ እውነተኛዋን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በምልኣት የሚወክል እንጂ - እውነተኛውን እምነቷን፣ አስተምህሮዋን፣ አምልኮዋን፣ . . . ሁሉ የሚገልጽና የሚያጠቃልል ነበር።
- ኦርቶዶክሳዊነት ጌታ የሰጠው፣ ሐዋርያት ያስተማሩት፣ አበው የጠበቁት ነው።
- ኦርቶዶክሳዊነት እውነተኛው ያልተበረዘውና በሰዎች ፍልስፍናዊ እርሾ ያልተበከለውና ያልተከለሰው እምነትና አስተምህሮ ነው።

ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ማወቅ ይቻላልን

- “መሰወሪያውን ጨለማ አደረገ” መዝ. 17፡11
- “ሰሎሞንም። እግዚአብሔር፦ በጨለማ ውስጥ እኖራለሁ ብሎአል . . . አለ።” 2 ዜና 6፡1-2
- “እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን፤ አሜን።” 1 ጢሞ. 6፡16
- “ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፥ ከወልድም በቀር ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም።” ማቴ. 11፡27 54
- “ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ መልእክት፦ እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት።” 1 ዮሐ. 1፡5

- “በፈጣሪና በፍጡር መካከል መጨረሻ የሌለው ሸለቆ (ጥልቀት) አለ።” ቅ. ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ
- “በፈጣሪና በፍጡር መካከል ማንም ሊያልፈው የማይችለው ክፍተት አለ።” ቅ. ኤፍሬም ሶርያዊ
- ይህ ጥልቅ ልዩነት ባሕርዩን የማወቅ 55
- ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ ጥልቅ ነገረ መለኮታዊ ትምህርቶችን ባስተማረባቸው በአምስቱ ተከታታይ ትምህርቶቹ (Theological Orations) ላይ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላል፡-

- ‘ኤልያስ ሆይ፣ በዚህ ምን ታደርጋለህ?’ የሚል ድምፅም ወደ እርሱ መጣ፤ ባሕርዩን [ያመለከተው] ግን አልነበረም። 1 ነገ. 19፡11-13
- የሶምሶን አባት ማኑሄ የእግዚአብሔርን መልእክተኛ (መልአክ) በማየቱ ብቻ እንኳ እግዚአብሔርን ማየት ይቅርና መልእክተኛውን ማየት እንኳ በሰዎች ዘንድ የሚቻል አይደለም ብሎ በማሰብ ‘እግዚአብሔርን አይተናልና ሞትን እንሞታለን’ እስከ ማለት ደረሰ። መሣ. 13፡22”
- (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናንዙ፣ አምስቱ ተከታታይ ነገረ መለኮታዊ ትምህርቶች)

- “መለኰታዊና ቅዱስ የሆነው ሕይወት [እግዚአብሔር] መለኪያና ስፍር የሌለው የመሆኑ ነገር ለማንኛውም ሰው ግልጽ ሊሆን ይገባዋል። እርሱ በጊዜ ውስጥ የሚኖር አይደለምና፣ ጊዜ ራሱ የተገኘው ከእርሱ ነው እንጂ። ፍጥረቱ ሁሉ ግን ከታወቀ መጀመሪያው ወደ ታወቀ ፍጻሜው ይሄዳል፣ በመካከልም በጊዜ በሚለኩ ሂደቶች ውስጥ ያልፋል፤ ስለዚህም ሰሎሞን እንዳለ (ጥበብ 7፡18) ለፍጥረታት መጀመሪያውን፣ መካከለኛውንና መጨረሻውን መለየት ይቻላል። ሩቅና ምጡቅ፣ ዘለዓለማዊና ቅዱስ፣ ሕያው ባሕርይ ለሆነው ለእርሱ ግን ስፍርም ሆነ ቦታ የለውም። የተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ ምንም እንኳ የሰው አእምሮ ውስንነት ሊደርስባቸው ላይችል ቢችልም እንኳ በፈጠራቸው በእርሱ ዘንድ የታወቁና የተሰፈሩ፣ በሥነ ፍጥረት ሀልወት ክበብ ውስጥ የታጠሩ ናቸው። ለተፈጠሩት ነገሮች ሁለ ዳርቻቸውንና ወሰናቸውን ያስቀመጠላቸው ፈጣሪ እርሱ ግን ገደብና ወሰን የለበትም፣

- ወሰን ወደ ሌለው ወደ እርሱ አኗኗር የሚደረጉ ፍለጋዎችንና የመለኰታዊ ባሕርይን ጥንት ምንነትና የትመጣነት ለመመርመር ከፍ ከፍ ብለው ሊወጡ የሚሞክሩትን አስተሳሰቦች ሁሉ እጅግ ይረቅባቸዋል፣ ባለመደረስ ውስጥም ይዘጋቸዋል። የጊዜን ድንበር በመሻገር በፊጣሪና በፍጡራን መካከል ካለው ባሕርያዊ ክፍተት (diastēma) አልፎ ለመሄድ የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ ሁሉ ያ ክፍተት ሊታለፍ የማይቻል መሆኑን ከሚያይበት ደረጃ ላይ ብቻ ይደርሳል፤ የሰው አእምሮና ሃሳብ መለኪያውና ወሰኑ ጊዜ (ho aiōn) እና በእርሱ ውስጥ ያለው ሌላው ነገር ሁሉ ነው። እነዚህን የሚያልፍ (ከእነዚህ ውጭ) የሆነ ነገር ሁሉ ለሰው አእምሮ ከዓቅሙ በላይና ሊደረስበት የማይችል ይሆንበታል።

- “የተፈጠረ ነገር ሁሉ አኗኗሩ (ህልውናው) በጊዜ እና በቦታ የተወሰነ ነውና። ዘለዓለማዊ በሆነው ህልውና ዘንድ ግን ጊዜም ሆነ ቦታ የለም፣ ራሱ ከራሱ ነው፣ ከእነዚህ በፊትና ውጭ ነው፣ በጊዜ የማይለካ ነው፣ ያለፈ እና የወደፊት በሚባሉ የጊዜ ጽንሰ ሃሳቦች የማይከፈል ነው፣ በእምነት ብቻ ልንረዳው የምንችለው ነው። ጊዜ ነክ የሆኑ ልምዶች በፍጥረት ውስጥ ላሉ ነገሮች ብቻ የሚሠሩና የሚኖሩ ናቸው። ሁሉ ነገር ዛሬ ለሆነለት ለዚያ ቅዱስና ገናና ህልውና ግን ያለፈውና የወደፊቱ በአንድ አምላካዊ የእውቀት ቅጽበት ጥላ ሥር ናቸው። . . . ከመጀመሪያ ሁሉ በላይ፣ ከጊዜ ውጭ የሆነው ህልውና እርሱ ለባሕርዩ ፍለጋ የለውም፣ የሚታወቀው ባሕርዩ ሊታወቅ የማይችል በመሆኑ ብቻ ነው።” (ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ፣ Against Eunomius, Book I, 36-37)

- የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማወቅን በተመለከተ ስለ መላእክት ሲናገርም እንዲህ ብሏል፡-
- “የመላእክት ኃይል ከእኛ ጋር ሲነጻጸር በማንኛውም መንገድ የበለጠ ሆኖ ይታያል። ሆኖም ሕያው ባሕርይ ከሆነው ከእርሱ ግናናነት ጋር ሲነጻጸር ግን የእነርሱ ታላቅነት እንኳ ከእኛ የእውቀትና የመረዳት ታናሽነት (ደካማነት) ያንም ያህል የበለጠ አይደለም የሚል ቢኖር ከእውነት የራቀ ነው ሊባል አይቻልም።
- “በፊጣሪና በፍጡራን መካከል ካለው ባሕርያዊ ርቀት (diastēma) ለእኛም ሆነ ለመላእክት የእግዚአብሔርን ባሕርይ በቀጥታ ለማወቅ የማይቻል ያደርግብናል። ቀንን ከኋላውና ከፊቱ እንደሚወስኑት ሁለት ሌሊቶች ፍጡራንን ከፊታቸውና ከኋላቸው ይወስናቸዋል።

- ጊዜና ቦታ ፍጡራንን ሊያልፉት በማይችሉት ወሰን ይከብባቸዋል። የሥነ ፍጥረትን መሪነት ልንከተል የምንችለው እስከዚያ ድንበር (መዳረሻ) ድረስ ብቻ ነው። ከዚያ ላይ ግን የሰው አእምሮ ያቆማል። የፊጣሪ ባሕርይ ከፍጥረቱ ሁሉ ሕሊና በላይ ነውና፣ መጀመሪያና መጨረሻም የለውምና፣ ከፍጥረት ውስጥ ተነሥቶ በሚደረግ ፍለጋና ጉዞም ሊደረስበት አይችልምና።” ለዩኖሚየስ ሁለተኛ መጽሐፍ የተሰጠ መልስ

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ

- “ብዙ የማውቃቸው ነገሮች አሉ፣ ሆኖም እንዴት ላብራራቸው (ልገልጻቸው) እንደምችል ግን አላውቅም። እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ እንዳለ (ምሉእ በኩለሄ እንደሆነ) አውቃለሁ። ሆኖም እንዴት ብሎ በሁሉም ቦታ እንደሚኖር ግን አላውቅም። ዘለዓለማዊ እንደ ሆነና መጀመሪያ እንደ ሌለው አውቃለሁ፤ እንዴት እንዲህ እንደ ሆነ ግን አላውቅም። አንድ በራሱ ህልው የሆነ ሕያው ህልውናውን ከሌላም ሆነ ከራሱ ሳይቀበል እንዴት ሊኖር እንደሚችል አእምሮዬ ለመረዳት አይቻለውም። እርሱ የባሕርይ ልጅ እንዳለው አውቃለሁ፣ እንዴት እንደ ሆነ ግን አላውቅም። መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ እንደ ሠረጸ አውቃለሁ፣ መንፈስ ቅዱስ እንዴት ብሎ ከእርሱ እንደ ሆነ ግን አላውቅም።

- “ዳዊት
- የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማወቅን በተመለከተ ባሰበ ጊዜ ማለት የቻለው ‘እውቀትህ ከእኔ ይልቅ ተደነቀች በረታች፣ ወደ እርሷም ለመድረስ አልችልም’ ነው። መዝ. 138፡6
- ነቢዩ ኢሳይያስ ፡- የእግዚአብሔርን ልደት መናገር የሚችል አለመኖሩን በማድነቅ ‘ወመኑ ይነግር ልደቶ - ልደቱን ማን ሊናገር ይችላል?’ በማለት በአግራሞት ይጠይቃል። ኢሳ. 53፡8 ቅዱስ ጳውሎስም የእግዚአብሔር ፍርዱ የማይመረመር፣ ለመንገዱም ፍለጋ የሌለው መሆኑን በማድነቅ ይናገራል። ሮሜ 11፡33
- ቅዱስ ጳውሎስ፡- እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ያዘጋጀው ሽልማት የማይመረመር ነው (ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው፣ በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደ ተጻፈ። 1 ቆሮ. 2፡9)፤ የእግዚአብሔር ሰላም አእምሮን ሁሉ ያልፋል (ፊል. 2፡9)፤ ስጦታውም ሊነገር አይችልም (2 ቆሮ፣ 9፡15)።

- ታዲያ የእግዚአብሔር ፍርዱ የማይመረመር፣ መንገዱ ፍለጋ የሌለው፣ ሰላሙ አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ፣ ስጦታው ሊነገር (ሊገለጽ) የማይችል፣ ለሚወዱት ያዘጋጀው ነገር በሰዎች ልቡና ያልታሰበ ከሆነ እነዚህ ከእርሱ የሚገኙት ነገሮች የማይመረመሩና የማይደረስባቸው ከሆኑ እነዚህን ያዘጋጀው ራሱ እግዚአብሔርማ ምን ያህል የማይመረመር ነው ይሆን! መናፍቃን ሆይ፣ የተፈጠሩት የማይታወቁ፣ የማይለጹና የማይመረመሩ ሲሆኑ እነዚህን የፈጠራቸው እርሱ ግን ይታወቃል፣ ይመረመራል ከማለት በላይ ምን እብደት አለ?

- “መላእክት በእግዚአብሔር መገለጥ ፊት ሲቆሙ ፊቱን እንኳ ማየት የማይችሉ ከሆነ ‘እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ላውቀው እችላለሁ’ ይል ዘንድ ሰው ማን ነው? . . . ወገኖቼ ሆይ፣ አርዮሳውያንን (አኖሚያኖችን) አእምሯቸው የታመመና የማሰብ ዓቅማቸውን በሕመም ያጡ ሰዎችን እንደምታዩ አድርጋችሁ ልትመለከቷቸውና ልታዝኑላቸው ይገባል። እግዚአብሔርን በባሕርዩ ላውቀው እችላለሁ ማለት ከአእምሮ መታወክ እንጂ ከጤና የሚመጣ አይደለምና።” ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ስለ

- አባ ሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም እንዲህ ይላል፡-
- “. . . ወኢርቱዕ እንከ ናስተማስሎ በእሳት ምድራዊ እሳትሰ ቦቱ መጠን ወቦቱ አካል ወመለኰትሰ ኢይትከሃል ይትበሃል ዘንተ የአክል ወዘንተ ይመስል - በምድራዊ እሳት እንመስለው ዘንድ አይገባም፣ ለእሳትስ መጠን አለው፣ ልክም አለው። መለኰት ግን ይህን ያህላል፣ ይህንም ይመስላል ሊባል አይቻልም።” ቁ. 47
- “አኮ ዘቦቱ ለመለኮት ክበብ ከመ ፀሐይ ወወርኀ ወዐቅም ከመ ሰብእ አላ መንክር ውእቱ ወንቡር ዲበ አርያሙ ጎበ ኢይበጽሖ ሕሊና ሰብእ ወኢዘመላእክት አእምሮ - ለመለኮት እንደ ፀሐይና እንደ ጨረቃ ክበብ፣ እንደ ሰውም መጠን ያለው አይደለም፣ ድንቅ ነው እንጂ፤ የሰው ሕሊና የመላእክትም አእምሮ በማይደርስበት በአርያሙ የሚኖር ነው እንጂ።” ቁ. 48

- “ወሶበ እኁሊ ዘንተ ይፈቅድ ሕሊናየ ይጽበት ዕመቀ አብሕርቲሁ ለወልድኪ ወያመዐብሎ መዋግደ ምሥዋራቲሁ ለፍቁርኪ ወሶበ እሔሊ ዘንተ ካዕበ ይፈቅድ ሕሊናየ ይዕርግ ላዕለ ወይጸእ በሥውር ወይቅላዕ መንጦላዕተ ምሥዋራቲሁ ለሕያው ወይፈርህ እምነደ እሳት ወኢይበጽሕ እስከ መጠነ መንፈቆሙ ለዐየራት - ይህንም ባሰብኩ ጊዜ ሕሊናየ የልጅሽን የባሕሩን ጥልቅነት ሊዋኝ ይወዳል፣ የወዳጅሽ የመሠወሪያው ማዕበልም ያማታዋል። ዳግመኛም ባሰብሁ ጊዜ ሕሊናየ ተሰውሮ ወደ ላይ ወጥቶ የሕያው መሠወሪያ የሆነውን ሊገልጥ ይወዳል፣ ከነደ እሳትነቱ የተነሣ ይፈራል፣ ከዐየራት ከእርቧቸው እርቦ አይደርስም።

- ወሶበ እሑሊ ዘንተ ይፈቅድ ሕሊናየ ይጸዐን መትከፈ ነፋሳት ወይስርር ምሥራቀ ወምዕራበ ሰሜነ ወደቡበ ወውስተ ኩሉ አጽናፍ ይርአይ ህላዌሆሙ ለፍጡራን ወይመጥን ዕመቃቲሆሙ ለአብህርት ያእምር ሉዐሌሁ ለሰማይ ወየአይይ እንተ በኩለሄ ወበኩሉ ይስእን ወይገብእ ኀበ ዘትካት ሉዐሌሁ - ይህንም ባሰብሁ ጊዜ ሕሊናየ በነፋስ ትካሻ ተጭኖ በምሥራቅና በምዕራብ በሰሜንና በደቡብ በዳርቻውም ሁሉ ሊበር ይወዳል። የፍጡራንን አኗኗር ያይ ዘንድ፣ የአብሕርትንም ጥልቀታቸውን ይለካ ዘንድ የሰማይ ርዝመቱን ያውቅ ዘንድ በሁሉ ዘንድ በሁሉም ይዞራል፣ አቅቶት ወደ ቀደመ አኗኗሩ ይመለሳል።
- ወይእዜኒ ኢንኅሥሥ ዕበያቲሁ ወኢንጠናቀቅ ማዕምቅቲሁ ዘኢይክል ልሳነ ነቢያት ወሐዋርያት ለወድሶተ መጠነ ዕበዩ - አሁንም ግናንነቱን አንመርምር፣ ጥልቅነቱንም አንጠናቀቅ፣ የግናንነቱን መጠን ለማመስገን የነቢያትና የሐዋርያት አንደበት የማይቻለው ነው።”

- Transcendent-ረቂቅነት፣ ምጡቅነት፣ ሩቅነት
- Immanent - ቅርብነት፣ አብሮነት
- “እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም። ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር።” ኤር. 23:23-24

- “ሙሴም እግዚአብሔርን እባክህ ክብርህን አሳየኝ አለው። ... እግዚአብሔርም፦ ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ። እነሆ ስፍራ በእኔ ዘንድ አለ፣ በዓለቱም ላይ ትቆማለህ፤ ክብሬም ባለፈ ጊዜ በሰንጣቃው ዓለት አኖርሃለሁ፣ እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ፤ እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፣ ጀርባዬንም ታያለህ፤ ፊቴ ግን አይታይም። ”

ዘጸ. 33፡17-23

- ፊት - ባሕርዩ
- ጀርባ - ?
- ስለዚህ የምናውቀው ባሕርዩን ሳይሆን ኃይሉንና ሥራውን ነው።

የእግዚአብሔርን መኖር የምናውቅባቸው መንገዶች

- 1) ሥነ ፍጥረት
- 2) አምላካዊ መግቦት
- 3) ሕሊና
- 4) በዚህ ዓለም የተፈጸመ የታሪክ ምስክርነት
- 5) መጽሐፍ ቅዱስ
- 6) የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ መገለጥ
- 7. በሃይማኖት

1) ሥነ ፍጥረት

- “ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ÷ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል። ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች÷ ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች።
- “ነገር የለም መናገርም የለም÷ ድምፃቸውም አይሰማም። ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ÷ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ።” መዝ. 18፡1-2
- “እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታዉቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ።” ሮሜ 1፡ 19-21

- “እግዚአብሔር በጊዜው ጊዜ በኋላ ዘመን በመጽሐፍ የሚያስጽፈውን አስቀድሞ በሥነ ፍጥረት መጽሐፍነት አስጽፎታል።” ጠርጠሉስ
- አንድ ፈላስፋ ቅዱስ እንጦንዮስን፦
- “በዚህ በረሃ ስትኖር ምን ታነባለህ? ከምንስ ትማራለህ?” ብሎ ጠየቀው፤ ቅ. እንጦንስም ሲመልስ፦ “ፈላስፋ ሆይ፣ የእኔ መጻሕፍት ሥነ ፍጥረት ናቸው” አለው።

2. አምላካዊ መግቦቱ

- “አቡየሂ እስከ ይእዜ ይገብር ወአነሂ እገብር” ዮሐ. 5፡17
- “እስመ ኩሉ እምኔሁ ወኩሉ በእንቲአሁ ወኩሉ ቦቱ ወሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን - ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።” ሮሜ 11፡36
- “በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን፤ እንኖርማለን።” የሐዋ. 17፡28

3. ሕሊና

- “ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ። ሮሜ 2፡14-15

4. በዚህ ዓለም የተፈጸመ የታሪክ ምስክርነት

- በዘመነ አበው
- በዘመነ መሳፍንት
- በዘመነ ነገሥት
- በዘመነ ነቢያት
- በዘመነ ሐዋርያት
- በዘመነ ሊቃውንት

5. መጽሐፍ ቅዱስ

- “እግዚአብሔር ይነግሮሙ ለሕዝቡ በመጽሐፍ” መዝ. 86:6
- “መጻሕፍት ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው።” ዮሐ. 5:39
- “ወወሀበ ሕገ ለረድኤት” ኢሳ. 8:20
- “አሁንም ሂድ፥ ለሚመጣውም ዘመን ለዘላለም እንዲሆን በሰሌዳ ላይ በመጽሐፍም ውስጥ ጻፍላቸው።” ኢሳ. 30:8 “ወበዝንቱ ኩሉ አስተርእዮ ኢረከበ ዓለም መድኃኒተ” ቅ. ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ (ሃ. አበው)

6. የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋዌ

- “በብዙኅ ነገር ወበብዙኅ መክፈልት አይድዐ እግዚአብሔር ለአበዊነ በነቢያቲሁ እምትካት
- ወመደኅረሰ መዋእል ነገረነ በወልዱ ዋሕድ ዘረሰዮ ወረሼ ለኩሉ -
- ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ኅዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን” ዕብ. 1፡1-2
- “በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።” ዮሐ. 1፡1-4

- “ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፥ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም፥ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ። በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።” ማቴ. 3፡16-17
- “እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።” ማቴ. 28፡19-20

- ሃይማኖታዊ ፍልስፍና
- እንደ አብርሃም ፡- አምላኩን ፍለጋ ከሚያየው ነገር ጀመረ ግን በእርሱ አቅምና ምርምር የሚታይ አምላክ ስላልሆነ አምላከ ፀሐይ ተናበበኒ አለ፤ አምላኩም ተገለጠለት ።
- በሃይማኖት ነአምር ከመ ተፈጥረ ዓለም በቃለ እግዚአብሔር ዕብ 11፣3
- ፍልስፍናዊ ሃይማኖት
- ማኒ፡- አምላኩን በእርሱ ቁሳዊ ነገር ልክ አደረገውና ያለ ባሕርዩ ስለፈለገው አልተገኘለትም አጀማመሩ የተሳሳተ ስለነበር የመጨረሻ ውሳኑውም የተሳሳተ ሆነ፤ ራሱንም ሳዳ

በነገረ ሃይማኖት ላይ ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች

- 1) ከተጻፈው አለማለፍ
- “ኢትጻኡ እምቃለ መጻሕፍት” 1 ቆሮ. 4፡6
- ያልተጻፈ አለመመርመር “ምሥጢሩ ግን ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው።” ዘዳ. 29፡29
- “እግዚአብሔርን የሚያምኑት በመልካም ሥራ በጥንቃቄ እንዲጸኑ፣ እነዚህን አስረግጠህ እንድትናገር እፈቅዳለሁ። ይህ መልካምና ለሰዎች የሚጠቅም ነው፤ ነገር ግን ሞኝነት ካለው ምርመራና ከትውልዶች ታሪክ ከክርክርም፣ ስለ ሕግም ከሚሆን ጠብ ራቅ፤ የማይጠቅሙና ከንቱዎች ናቸውና፤ መለያየትን የሚያነሣ ሰው ጠማማ እንዲሆን በራሱም ላይ ፈርዶ ኃጢአትን እንዲያደርግ አውቀህ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜም ከገሠጽኸው በኋላ እንዲህ ከሚመስል ሰው ራቅ።” ቲቶ 3፡8-11
- “አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ” 2 ጢሞ. 4፡4

ዓላማችንን ማወቅ

- ነገረ ፅንሠቱ
- ነገረ ልደቱ ...
- “ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም።” 1 ቆሮ. 3፡2 “እግዚአብሔር በሰማይ አንተም በምድር ነህና በአፍህ አትፍጠን፣ በእግዚአብሔርም ፊት ቃልን ይናገር ዘንድ ልብህ አይቸኩል፤ ስለዚህም ቃልህ ጥቂት ትሁን።” መክ. 5፡6

እግዚአብሔር እናውቀው ዘንድ ግልጽ ያላደረገውን ማወቅ

- የመልከ ጼዴቅ የዘር ሐረግ - ዕብ. 7፡1-3
- የዓይንዶሯ ሴት ያስነሣችው ማንን ነው? 1 ሳሙ. 28
- ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ተነጠቀ፣ - እስከ የት ነው? እንዴት? ሦስቱ ሰማያት እነ ማን ናቸው?... 2 ቆሮ. 12፡1-5
- “ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፣ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ፣ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።” 1 ቆሮ. 13፡12
- ሰባቱ ነጎድጉአድ የተናገሩትን ሰማሁ ልጽፈውም ወደድሁ፤ከዚህም በሁአላ ሰባቱ ነጎድጉአድ የተናገሩትን በምሥጢር ጠብቀው አትጻፈውም የሚል ቃል ከሰማይ መጣ ። ዮሐ 10፣4

- ዮሐ. 20፡30-31 ጌታችን ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ብዙ ሌላ ተአምራት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ። ነገር ግን ይህ የተጻፈ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሐየር ልጅ እንደሆነ እናንተ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ የዘለዓለም ሕይወትን ታገኙ ዘንድ ነው።

አንድ ጥቅስ ላየይ ብቻ አለመንጠልጠል

- ለእመ ረከብከ ቀለመ ጸዋግ ተመየየጥ ቦቱ ዐሠርተ ወክልኤተ ጊዜያተ
- አንብብ ለዛቲ መጽሐፍ እምጥንታ እስከ ተፍጸሜታ
- (ምክረ አበው)

አዕማደ ምሥጢር

- ምሥጢረ ሥላሴ
- ምሥጢረ ሥጋዌ
- ምሥጢረ ጥምቀት
- ምሥጢረ ቁርባን
- ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

ምሥጢረ ሥላሴ

- የሥላሴን ልዩ አንድነት ሦስትነት
- የሥላሴ አንድነት፡- በሥልጣን፣ በመለኮት፣ በባሕርይ፣በአገዛዝ፣ወዘተ
- የሥላሴ ሦስትነት፡- በስም ፣በግብር፣ በአካል
- የኩነታት ሦስትነት፡- አብ-ልብ ፣ወልድ-ቃል፣ መንፈስ ቅዱስ -ሕይወት፣እስትንፋስ

የምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌዎች

- የፀሐይ ሦስትነት፡- ክበቡ፣ብርሃኑ፣ሙቀቱ
- አብ ፀሐይ፣ ወልድ ፀሐይ፣መንፈስ ቅዱስ ፀሐይ አሐዱ ውእቱ ፀሐየ ጽቅድ
- የእሳት ሦስትነት፡- አካሉ፣ ብርሃኑ፣ ሙቀቱ
- አብ እሳት፣ ወልድ እሳት ፣መንፈስ ቅዱስ እሳት፣ አሐዱ ውእቱ እሳተ ሕይወት ዘእምአርያም
- የነፍስ ሦስትነት፡- አብ- ልብ ፣ወልድ- ቃል ፣መንፈስ ቅዱስ -እስትንፋስ

ምሥጢረ ሥጋዌ

- ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ በተለየ አካሉ በተወላዲነት ግብሩ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም መወለዱን፤ በሕማሙ፤ በመስቀሉ፤ በሞቱ ዓለምን ማዳኑን የምንማርበት

ለምን ሰው ሆነ

- አራያ ለመሆን፡-
- አራያነት በተግባር የሚገለጽ ስለሆነ
- ሰውን ለማዳን፡-
- ሰው መሆን ነበረበት ፡- የበደለው ሰው ነውና
- መሞት ነበረበት፡- በበደለኛው ላይ የተፈረደው ሞት ነበርና
- ሞት መሸነፍ ነበረበት፡- ሞት ካልተሸነፈ ዓለም አይድንምና
- ንጹሐ ባሕርይ መሆን ነበረበት፡- በራሱ ኃጢአት ሞተ ያስብላልና

የምሥጢረ ሥጋዌ ምሳሌዎች

- የሥጋና የነፍስ ተዋሕዶ
- የብረትና የእሳት ተዋሕዶ

በምሥጢረ ጥምቀት

- ካህኑ ውሃውን ሲባርከው ማየ ገቦ መሆኑን፤
- የተወሰደብንን ልጅነት የምናገኝበት መሆኑን
- ከሥላሴ ብርሃን ለብሰን ብርሃን ተጎናጽፈን የምንወለድበት መሆኑን
- ሁለተኛ ልደት፡- ዮሐ3፣5
- ድኅነታችን እውን የሚሆንበት ነው። ማር 16፣16 የአመነ የተጠመቀ ይድናል።

ምሥጢረ ቁርባን

- ሥጋየን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው ዮሐ6፣50-
- ከክርስቶስ ጋር አንድ ኅብረት የምንሆንበትን
- ከፈለነ ንብላዕ እምዕፀ ሕይወት ዘውእቱ ሥጋሁ ወደሙ በእንተ ፍቅረ ዚአነ

ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

- ዘለዓለማዊ ሕየወትን የምንወርስበት መሆኑን
- ዳግመኛ የምንነሣበትን ምሥጢር
- ትንሣኤ ዘጉባኤን
- ማዕረሩሰ ጎልቀተ ዓለም ውእቱ ወአጸዱኒ እሙንቱ መላእክት እምበለስ አእምሩ አምሳሊሁ እምከመ ለምለመ አእጹቂሁ ይፈንዎሙ ለመላእክት በቃለ ኃይሉ። (ቅ/ያሬድ)
- አመ ይመጽእ ንጉሥ በግርማ መነግሥት ኩነኔ ድልው ቅድሜሁ ነፍስ ትርእድ ወመጻሕፍት ይትከሰታ ለስምዕ (ቅ/ያሬድ)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር